# የልዩ ፍላጎት አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 87/2013

Special Needs Inclusive Education Strategy Implementation Guide (Directive No. 87/2013)

ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Education

ኅዳር 1፥ 2013

ገፅ

1. መግቢያ…………………………..……………………………………………..1

1.1.

ዳራ………………………………………………………………………...1

1.2. የመሜያው አስፈላጊነት………………………………………………………2

2. የመሜያው ዓላሜዎች……………………………………………………………3

3. የቁልፍ ቃላት ትርጉም………………………………………………………………3

3.1. ልዩ ትምህርት…………………………………………………………………3

3.2. ልዩ ፍላጎት ትምህርት……………………………………………………..4

3.3. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተሜዎች………………………………………………4

3.4. አካቶ ትምህርት……………………………………………………………...5

3.5. መቀላቀል……………………………………………………………………….6

3.6. ተዘዋዋሪ ማህራን …………………………………………………..………..6

3.7. ድጋፍ ማስጫ ሜከላት…………………………………………………………..6

4. አካቶ ትምህርትን በሜስፋፋት ሂደት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሜ......................7 5. በትምህርት ስርዓቱ የተለያዩ አካላት የስራ ድርሻና ሃላፊነት.............................9

5.1. ፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር……………………………………………………...9

5.2. የክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ……………………..……………11

5.3. የክልል/ከተማ አስተዳደር የቴ/ሙ/ት/ስ/ ኤጀንሲ…………………………………13

5.4. የዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት ማሜያ ………………………...……………..15

5.5. የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት………………………………………………………15

5.6. የወረዳ/ቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ…………………………………………..17

5.7. ትምህርት ቤት…………………………………………………………………..18

5.7.1. የትምህርት ቤት አስተዳደር……………………..……………………..18

5.7.2. የሜደበኛ ትምህርት ማህር……………………..……………………..21

5.7.3. ድጋፍ ማስጫ ሜከል……………………………………………………22

5.7.3.1. ተዘዋዋሪ

ማህር……………………………………………………..22

5.7.3.2. የስነ-ልቦና ባለሙያ (ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት).................................23
5.7.3.3. ብሬል አሰልጣኝ (ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት).............................23
5.7.3.4. የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ...........................................23
5.7.3.5. የልዩ ት/ቤት/ ክፍል/ መምህር.........................................24
5.7.3.6. ወላጆች..............................................................24
5.8. የጎልሞች ማሰልጠኛ ጣቢያዎች.................................................24
5.9. የቴ/ሙ/ት/ስ/ ኮለጅ...............................................................25
5.10. ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ................................................................25
6. የባለድርሻ አካላት ሚና.................................................................27
6.1. የአካቶ ትምህርት ብሄራዊ አማካሪ ኮሚቴ.........................................27
6.2. የሚኒስትር መ/ቤቶች..............................................................27
6.3. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መ/ቤቶችና ሞያዎች...............................28
6.4. የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሄራዊ ማህበር.......................................28

# 1. መግቢያ

## 1.1. ዳራ

ትምህርት ማኅረታዊ ሰብዓዊ መብት ነው፡፡ ዘላቂነት ያለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ዕውን ለማድረግ የሚያስችልም ትክ የለሽ መሳሪያ ነው፡፡ ይህንን ዕውነታ የተገነዘበው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በፆታ፤ በአካላዊ ሁኔታ፤ቋንቋ፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፤ ሃይማኖት፤ ወዘተ ልዩነቶች ያልተገደበ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ ለማድረግ በቁርጠኛነት እየሰራ ይገኛል፡፡ አካል ጉዳተኞች እንደ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ የትምህርትና ስልጠና አገልግሎቶች ዕኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን ከሚረጋገጥ አኳያ መንግስት የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን ቀርፆ ስራ ላይ ማዋሉ የቁርጠኛነቱ አንድ ማሳያ ነው፡፡

በዚህ ማኅረት የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ትምህርት የሁሉም ዜጎቸ መሆኑን ከሚረጋገጥም በላይ ባለፉት መንግስታት ከልማት ተገልልው ለኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የፌደራል መንግስት ልዩ የሀብትና የሙያ ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው ይደነግጋል፤ በተለይም የህገ መንግስቱ አንቀፅ 41 እና 91 መንግስት የሜሎ ማቋቋሚያና የድጋፍ አገልግሎቶችን ለአካል ጉዳተኞች የማቅረብ ሃላፊነት እንዳለበት ይገልፃሉ፤ ከዚህም በላይ፤ መንግስት ከአካቶ ትምህርት ጋር አግባብነት ያላቸውን ልዩ ልዩ ዓለም ዐቀፍ ድንጋጌዎች፤ ኮንቬንሽኖችና ደንቦች በተለይም ለአካቶ ትምህርት አፅንኦት የሰጠውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን የ2006 (እኤአ) የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ኮንቬንሽንን ተቀብሎ በማፅደቅ የአገሪቱ ህገ መንግስት አካል እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

በተመሳሳይ በ1986 ዓ.ም ፀድቆ በተግባር ላይ የዋለው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ጥራት ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ማዳረስ የመብት ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ልማትን የሚያረጋግጫ ዋስትና መሆኑን በሚያሻማ ሁኔታ ይገልፃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፖሊሲው ትምህርት ያለ አንዳች አድልዎ ለሁሉም ህፃናት እንደሚሰጥና ከትምህርት ዘርፍ ልማት ተገልለው ለኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ድጋፍ እንደሚደረግ ያረጋግጣል፡፡ የአካል ጉዳተኞች ትምህርትን በተመለከተም ፖሊሲው፤

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ከፍላጎታቸውና ከዕምቅ ችሎታቸው ጋር የተጣጣመ ትምህርት እንደሚሰጣቸው (ቁጥር 2.2.3)፤
- ለልዩ ፍላጎት ትምህርት የሚያስፈልጉ የድጋፍ ግብዓቶች እንደሚሟሉ (ቁጥር 3.7.6) እና
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያዎች በመደበኛው የመምህራን ትምህርት ፕሮግራም እንደሚሰለጥኑ (ቁጥር 3.4.9.) በግልፅ ያመለክታል፡፡

የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን መሰረት በማድረግም ትምህርት ሚኒስቴር ትምህርትን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናትና ለተዘነጉ የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጂ በ1998 ቀርፆ እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ተግባራዊ እንዲሆን አድርጓል፤ ስትራቴጂው በስራ ላይ በዋለባቸው 5 ዓመታት ከተገኙ ጥቂት ወጤቶች መካከልም የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራሞች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መጀመራቸው፤ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች መካሄዳቸው፤ የተወሰኑ ሪሶርስ ማዕከላት መቋቋማቸውና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መከናወናቸው ለአብነት ያህል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ይሁንና ስትራቴጂው በነበሩት ወስጣዊ ደካማዎችና በትግበራ ወቅት ባጋጠሙ ችግሮች ምክንያት የታለሙትን ግቦች ማሳካት አልቻለም፡፡

ስለሆነም፣ ትምህርት ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ የ1998ቱን ስትራቴጂ በማሻሻል የተጠናከረ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራተጂ በ2004 ዓ.ም. ነድፏል፡፡ በቀጣይነትም ስትራቴጂውን ስራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ ይህን የአተገባበር መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

## 1.2. የመመሪያው አስፈላጊነት

የ2004ቱ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አጠቃላይ ዓላማ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ህፃናት፤ ወጣቶችና ጎልማሶች ጥራትና ተገቢነት ያለው እንዲሁም ፍትሃዊ የሆነ ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኙ የሚያደርግና በሂደትም እነዚህ ዜጎች በአገራቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ወስጥ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል የአካቶ ትምህርት ስርዓት ማንባት ነው፡፡ ይህን ዓላማ ዕውን ከማድረግ አኳያም ስትራቴጂው ዘርፈ-ብዙ ስትራቴጂያዊ

አቅጣጫዎችን አካቷል፡፡ ነገር ግን፤ ስትራቴጂው የታለማትን ግብ ማሳካት የሚቻለው በተሟላና በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ ሲደረግ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግም በትምህርት ስርዓቱ ወስጥ ያሉ ተዋናዮችና ከትምህርት ስርዓቱ ውጭ ያሉ ባለድርሻ አካላትን ያልተቆጠበና የተባበረ ጥረት ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም፣ ይህ መመሪያ የእያንዳንዱን ፈፃሚ ሃላፊነቶችና ግዴታዎች እንዲሁም የተባባሪ ድርጅቶችን የስራ ድርሻ ለይቶ የሚያስቀምጥ ሰነድ በመሆኑ ለስትራቴጂው የተሟላ ትግበራ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

# 2. የመመሪያው ዓላማዎች

ይህ መመሪያ የሚከተሉትን ዓላማዎች በማሳካት ላይ ያተኩራል፤

- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ዙሪያ ያሉ ዋና ዋና ፅንስ ሃሳቦችንና የአተገባበር ልምዶችን ግልፅነት ባለው መልኩ በአከናዋኞች ወስጥ በማስረፅ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበር በዕውቀት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ፤

- ከስትራቴጂው ትግገበራ አኳያ በትምህርት ስርዓቱ ወስጥ ያሉ ፈፃሚዎች ተጠየቂ የሚሆኑባቸዉን የነፍስ–ወከፍና የጋራ ሃላፊነቶችና ግዴታዎች በግልፅ ማስቀመጥ፤
- ከትምህርት ስርዓቱ ውጭ ያሉ ባለድርሻ አካላትን የነፍስ–ወከፍና የጋራ ሚናዎች ማዘርዘር፤
- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ወጥነት ባለዉና ስታንዳርዱን በጠበቀ ሁኔታ በመላ አገሪቱ እንዲተገበር ማድረግ፤

# 3. የቁልፍ ቃላት ትርጉም

## 3.1. ልዩ ትምህርት (Special Education)

ልዩ ትምህርት  ለአካል ጉዳተኞችና የማህበራዊና ስሜታዊ ችግሮች ወዘተ ያሉባቸው ተማሪዎች በልዩ የመማሪያ ክፍሎች፤ በዩኒቶችና በልዩ ትምህርት ቤቶች በተለየ ሁኔታ ለማገዝ የሚደረግ  የትምህርት አደረጃጀትን ያጠቃልላል፡፡ በነዚህ ትምህርት ቤቶችም ሆነ የመማሪያ ክፍሎች የሚያስተምሩ መምህራንም እነዚህን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ለመርዳት የተለየ ስልጠና የወሰዱ ሲሆን ተማሪዎችም የተለያዩ ባለሙያዎችን እንደ ቴራፒስቶች የመሳሰሉትን የማግኘት ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ የተማሪ– መምህር ጥምርታውም ከመደበኛው ትምህርት ያነሰ ነው፡፡

## 3.2. ልዩ ፍላጎት ትምህርት (Special Needs Education)

ልዩ ፍላጎት በማለት ልዩ ትምህርትን ተክቶ የመጣ አደረጃጀት እንጂ ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው ፅንሰ–ሃሳቦች አይደሉም፡፡ ይልቁንም፤ ለአካል ጉዳተኞችም ሆነ የማህበራዊና ስሜታዊ ችግር ያሉባቸዉን ጨምሮ የመማር ችገሮች ያሉባቸዉን ተማሪዎች ለማገዝ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ሁሉ ያካትታል፡፡ ይህም በልዩ ትምህርት ቤቶችና በልዩ የመማሪያ ክፍሎች ከሚሰጡ የትምህርት ድጋፎች ጀምሮ በማካተት የሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፡፡

## 3.3. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች (Learners with Special Educational Needs)

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የምንላቸው በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ የመማር ችግሮች የሚያጋጥማቸዉንና በዚህም ሳቢያ የአጭርና የረዥም ጊዜ ተጨማሪ ድጋፍን የሚሹ ተማሪዎችን በሙሉ የሚያጠቃልል ሲሆን፤ በሌላ አገላለፅ እነዚህ ተማሪዎች የመማርና የዕድገት እንቅፋቶች የተጋረጠባቸው ልጆች ናቸው፡፡ እነዚህን ተማሪዎች የጥቅም ተጋሪ እንዳይሆኑና ከትምህርቱ እንዲገለሉ የሚያደርጓቸው በርካታ ምክንያቶች ሲኖሩ በጥቂቱ ለመጥቀስም፤

- አካል ጉዳተኝነትና ማህበራዊና ስሜታዊ ችግሮች
- ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ
- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዝቅተኝነትና ተያይዞ የሚመጡ የተመጣጠኑ ምግብ እጥረቶች
- ኤችአይቪ ኤድስ
- አናሳ ብሄረተኝነትና ባህላዊ ተፅዕኖ
- ብቸኝነትን የተላበሰ ገጠራማ ኑሮ
- የተለያዩ ጦርነቶችና ግጭቶች ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ምንም እንኳን በሰነዱ ላይ የተጠቀሱት ሮሆዎች ከላይ በተጠቀሱት ችግሮች ሰለባ የሆኑትን ልጆች በሙሉ የሚጠቃልል ቢሆንም፤ ዋነኛ ትኩረቱ ባሁኑ ሰዓት ከትምህርት ገበታ ውጭ በሆኑና በርካታ ቁጥር ባላቸው አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችና የማህበራዊና ስሜታዊ ችግሮች ተጠቂ በሆኑት ተማሪዎች ዙሪያ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ ማታወቅ የሚገባው ጉዳይ ከላይ ከተገለፁት ችግሮች አንዱ በሌላኛው ችግር ላይ በተደራቢነት በማከሰት ተማሪወን የጣምራ ችግር ሰለባ ሊያደርገው እንደሚችል ነው፡፡ ለምሳሌ፤ ከአካል ጉዳተኝነት በተጨማሪ በማህበራዊና ኢኮኖሚ ዝቅተኝነት ሳቢያ በብቸኝነትና በገጠራማ አካባቢ ለመኖር የማደድ አጋጣሚ በተማሪው ላይ ሊፈጠር ይችላልና፡፡

## 3.4. አካቶ ትምህርት (Inclusive Education)

በዩኔስኮ (እ.ኤ.አ. 2005) አገላለፅ "አካቶ ትምህርት የትምህርት ስርዓቱን በማጎልበት ትምህርትን ለሁሉም ልጆች ለማዳረስ የሚደረግ ሂደት ነው..." እንደ አጠቃላይ ሮህ ሁሉንም የትምህርት ፖሊሲዎችን ተግባራት በማምራት ትምህርት ማዕረታዊ የሰው ልጆች መብት መሆኑንና የበለጠ ፍትሃዊና በዕኩልነት የተማሰረተ ህብረተሰብ ለመፍጠር ማሰረት በመጣል ይጀምራል፡፡ ስለዚህም አካቶ ትምህርት በደህነት፤ በስርዓተ ፆታ፤ በዘር፤ በቋንቋ ወይም በአካል ጉዳት ልዩነት ሳያደርግ ሁሉንም ተማሪዎች የሚስተናገድ ዝግጁ የሆነ የትምህርት ስርዓት መሆኑን ማገንዘብ ይገባል፡፡

አካቶ ትምህርት ሁሉም ልጆችና ተማሪዎች ሊማሩ ይችላሉ ብሎ ያምናል፡፡ በዚህ የትምህርት አቀራረብ በትምህርት ቤቶች ፤ በሙያ ማሰልጠኛ፤ በከፍተኛ ትምህርት፤ በማህራን ትምህርትና በትምህርት ቤት የትምህርት አሜራር ወስጥ የትምህርት ቅስማሽ እንቅፋቶችን ማለየትና እነዚህን እንቅፋቶች መቀነስ ወይም ማስወገድ አስፈላጊና የሚታለፍ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፤ አካቶ ትምህርት ለማለልና ዝቅተኛ ወጤት ለማስማዝገብ ተጋላጭ ለሆኑ ተማሪዎች ትኩረት ይሰጣል፡፡ በዚህ የትምህርት አሰጣጥ የትምህርት ከባቢው የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎቶች ለማስተናገድ ማጣማት እንደሚኖርበት ግድ ይላል፡፡ ይህም ማለት፤ ምቹ የመማሪያ ከባቢ ካለና ድጋፍ ከተደረገላቸው ሁሉም ልጆች ይማራሉ የሚለውን የአካቶ ትምህርት ማዕረታዊ

ግምት ማሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህም በትምህርት ቤቱና በስርዓቱ ላይ ሁሉንም ልጆች በሚያስተናግድ መልኩ ተግባራዊ ለውጥ ለማምጣት ማለትም በትምህርት ቤቱ
ማህበረሰብ አመለካከት፤ በማስተማር ዘደዎች ማሻሻል፤ በትምህርት ግብዓቶች አቅርቦት፤ በስርዓተ ትምህርት ማሻሻል፤ የትምህርት ቤቱን ከባቢና ግልጋሎቶችን ተደራሽ ማድረግን ያመለክታል፡፡

## 3.5. መቀላቀል (Integration)

በአካቶ ትምህርት አቀራረብ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ድጋፍ እየተደረገላቸው ሙሉ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በመደበኛው ክፍል ወስጥ ሲሆን በመቀላቀል አቀራረብ ግን እነዚህ ተማሪዎች በመደበኛው ክፍሎች ወስጥ እንዲማሩ ለሙሉ ቀን ወይም ለግማሽ ቀን (ለተወሰነ ጊዜ) ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ በቀሪው የትምህርት ጊዜያቸው በልዩ ክፍል ወይም ዩኒት ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ በአንዳንድ አገሮች መቀላቀልን የአካቶ ትምህርት ሙሉ ትግበራ ከመካሄዱ በፊት እንደ ሽግግር ወቅት ይጠቀሙበታል፡፡

## 3.6. ተዘዋዋሪ/ተንቀሳቃሽ መምህር (Itinerant Teacher)

ተዘዋዋሪ መምህር በልዩ ፍላጎት ትምህርት የተማረ ባለሙያ ሲሆን ለመደበኛ መምህራን ፤ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችና ለወላጆች የምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የሚሰጠውም አገልግሎት፤ የተማሪወን የነፍስ-ወከፍ የትምህርት መርሀ-ግብር ትግበራን፤ የተማሪወን የትምህርት ፍላጎት ምዘናን ከሳተላይትና ከጎረቤት ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ-መምህራንና መምህራን ጋር ትብብር መፍጠርን ፤ የልጁን የትምህርት ግቦች ለማሟላት ሌሎች ባለሙያዎችንና ወኤሻዎችንነ ማስተባበር፤ በተማከለ ቡድን (core team) ተግባራት ወስጥ ማሳተፍና የማሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

## 3.7. የድጋፍ ማሰጫ ማዕከል (Resource Center)

የድጋፍ ማሰጫ ማዕከል ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ማልገያ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን፤ የአካል ድጋፍ ማሰጫ ማሳሪያዎችንና ለሁሉም ተማሪዎች የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ ማሳሪያዎችን የያዘ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህ ማዕከል ልዩ ፍላጎት ያላቸወን ተማሪዎች፤ ለመደበኛ መምህራንና ለአጎራባች ትም/ ቤቶች ድጋፍና የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ይይዛል፡፡

# 4. አካቶ ትምህርትን በማስፋት ሂደት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሚና

አካቶ ትምህርትን ዕወን በማድረግ ሂደት በርካታ ማሳናከሎች እንዳሉ ቢታወቅም ለአብነት ያህል ሁለቱን ብቻ መጠቆም ይበቃል፤

1) በርካታ ህፃናት አሁንም ከትምህርት ገበታ ውጭ መሆናቸው፤

2) ተካተው ከሚኙ በርካታ ህፃናት መካከልም ተገቢውን እገዛ ካለማግኘታቸው የተነሳ ከትምህርት ቤት ለማቋረጥ የሚገደዱ መበዛታቸው ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በአገራችንም የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳይ እነዚህን ማሳናከሎች ከመቋቋም ጋር የተገናኘ ነው፡፡ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ርዕይም በዚህ ረገድ ግንዛቤን በማስፋት አካል ጉዳተኛ ልጆች ወደ ትምህርት ገበታ የሚጣጡበትን መንገድ መሻት ነው፡፡ ከስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች አንዱና ዋነኛውም የትምህርትን ዕገዛ አድማስ ለማስፋት ለሁሉም የመደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ፅንሰ-ሃሳብ ዙሪያ ስልጠና መስጠትና ባሉት የድጋፍ ማስጫ ማዕከላትም የተጠናከሩ መዋቅሮች በማዘርጋት ተዘዋዋሪ መምህራንን የማስማራት ተግባር ለክናወን ይገባል፡፡ በመሆኑም፣ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ሜ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ላይ ሊያተኩር ይገባል፤

- የልጆችን ችግር የማለየትና የመመዝን ስራ ማከናወንና አስፈላጊውን ድጋፍ በልዩ የመሜያ ክፍሎችም ሆነ በመደበኛ የመሜያ ክፍል የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት፤
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተሜዎች ተገቢውን እገዛ ማገዝ የሚቻልበትን መንገድ ማመቻቸት፤
- የመሜር ማስተሜኡ ስርዓት ሁሉንም ልጆች ማገዝ የሚቻልበትን መንገድ ማመቻቸት፤
- ሁሉም ህፃናት መብታቸው ተከብሮ ተገቢውን ትምህርት ማግኘት ይችሉ ዘንድ የአጠቃላይ ትምህርት ስርዓቱንና የክፍል ወስጥ ስርዓቱን በተገቢው መንገድ ሜደራጀት፤
- የትምህርት ጥራትን ከማስደግ አኳያ ለትምህርት ለሁሉም ግብ ስኬት የበኩሉን አስተዋፅኦ ሜድረግ ናቸው፡፡

**በስትራቴጂው ወስጥ የተካተቱት አቀራረቦችም በ3 መንገዶች ለተሜዎች እገዛ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡**

1) በመደበኛው የመሜር ስርዓት ወስጥ የሚገኙ አብዛኞቹ ተሜዎች በድጋፍ ማስጫ ማዕከል ከሚሰሩ ተዘዋዋሪ መምህራን ዕርዳታ በሚያገኙ የመደበኛ ትምህርት መምህራን ሊታገዙ ይገባል፡፡ በመሆኑም፣ የድጋፍ ስርዓቱ ትምህርት ቤት ዐቀፍና መሜያ ክፍል ዐቀፍ ሆኖ የተዘዋዋሪ መምህራንን ድጋፍ በማጠቀም ብዝሀ-ፍላጎት ያላቸውን ተሜዎች እንዴት ማገዝ እንደሚቻል፤ በርካታ ተሜዎች ባሉበት የመሜያ ክፍል ወስጥ ድጋፍ አሰጣጥን፤ የአቻ ለአቻ ድጋፍን አስፈላጊነትንና የመሳሰሉት የተካተቱበት ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት አቀራረብ ስልቶች በመደበኛው የማስተሜያ ክፍል ወስጥ ሊተገበሩ የሚቻሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም፣ በማስተሜር ስልቶች የታጠቁ ተዘዋዋሪ መምህራን ባሉበት ትምህርት ቤት የሚገኙ መደበኛ መምህራን ብዝሀ- ፍላጎት ያላቸውን ተሜዎች የማገዝ ልምዳቸው የዳበረ ይሆናል፡፡

2) ሁለተኛው ጉዳይ የሚያተኩረው ለመማር ችግር አደጋ (risk) የተጋለጡ ተማሪዎችን በመደበኛው የማስተማሪያ ክፍል ወስጥ ድጋፍ የማስጠትን ይመለከታል፤ በመደበኛው የማስተማሪያ ክፍል ያሉ ማምህራን ተዘዋዋሪ ማምህራንን በማማከር፤በክፍል ወስጥ ተጨማሪ እገዛ፤ ቅርብ ክትትልና የድጋፍ ማስጫ መሳሪያዎችን በሚፈላለግ የመማሪያ ክፍሎችን ለመማር ምቹ ማድረግን ያካትታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አግባብነት ያለው ትምህርታዊ ጣልቃ ገብነት (educational intervention) ለተዘዋዋሪ ማምህሩም ሆነ ለመደበኛው ክፍል አስተማሪ ችግሮችን በመቅረፍ መፍትሄ ለማስጠት የሚያስችል ድጋፍ እንደሚሆነው ማንዘብ ያሻል፡፡

3) የሚጨረሻወና የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት የድጋፍ አሰጣጥ ከፍተኛ የመማር ችግርና የአካል ጉዳት ያለባቸወን ተማሪዎች የሚመለከት ሲሆን እነዚህ ህፃናት ጥልቀት ያለው እገዛ እንደሚሹ ያሳያል፡፡ ይህም እገዛ በትናንሽ ቡድኖች በሚደራጀት የሚከሄድን የትምህርት አሰጣጥ የሚያካትት ሲሆን በሰለጡኑ ማምህራንና የተለየ የመማሪያ አካባቢ (በጉድኝት ማዕከላት፤ የተለየ የመማሪያ ክፍል፤ በሌሎች የትምህርት ተቋማት፤ ወዘተ) ተመቻችተውላቸው ቢሆን ይመረጣል፡፡ ጥቂት የሚሆኑት ደግሞ በልዩ ትምህርት ቤቶች እንዲታገዙ የሚደረግ ሲሆን፤ እነዚህም ትምህርት ቤቶች ለአጎራባች ትምህርት ቤቶች ሳይቀር ልዩ ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችን ሊያገለግሉ የሚቹሉ የድጋፍ ማስጫ ማዕከላት እንደሚሆኑም ከግምት ወስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

# 5. በትምህርት ስርዓቱ ወስጥ የተለያየ የትምህርት ደረጃዎች የስራ ድርሻና ሃላፊነት

## 5.1. ፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር

- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ተግባራትን በፌደረል ደረጃ ለመተግበር ያቅዳል፤ በቂ በጀትም ይመድባል፤
- የአካቶ ትምህርት መርሆዎች ተገቢነት ባላቸው በሁሉም የትምህርት ዘርፍ ዕቅዶች በጀትና የማምህራን ልማት መርሀ ግብር ወስጥ መካተታቸወን ያረጋግጣል፤
- የክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ለሁሉም ልጆች አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ትምህርት ለማስጠት ዕቅድ ማውጣታቸወንና በጀት መመደባቸወን ይከታተላል፤
- ማምህራን በስራ ላይ ሊጠቀሙበት የሚረዳቸው በቂ ዕቀወቀትና ክህሎት ለማስጨበጥ ይቻል ዘንድ በማምህራን ትምህርት መርሀ ግብሮች ተገቢ ኮርሶችን ይከልሳል፤
- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ላይ የሚሰጡ ኮርሶች ብቃት ባላቸው የትምህርተ ዘርፉ ባለሙያዎች ማስጠታቸወን ይከታተላል፤

- ከክልል የትምህርት ቢሮዎችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር አካቶ ትምህርትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ መመሪያዎችን፤ ስታንዳርዶችንና ቁሳቁሶችን ያዘጋጃል፤ ለምሳሌ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች ለመለየት የሚያገለግል የመለያ መሳሪያ፤ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሀ ግብር፤ ስርዓተ ትምህርትንና የምዘና መሳሪያዎችን ማስማማት፤ ወዘተ
- ተካተው በትምህርት ቤት ወስጥ በመማር ላይ ያሉትን ልዩ ፍላጎት ያላቸውንና ወይም አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን መረጃ ለማሰባሰብ /ለማግኘት ይቻል ዘንድ ብሄራዊ/ አገር ዐቀፍ የመረጃ ቋት ስርዓት ማዘርጋት/ ማቋቋም፤
- ከክልል/የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎችና ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር የአካል ድጋፍ መሳሪያዎችንና ሌሎች የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበር ላይ ድርሻ ካላቸው የተለያዩ አጋሮች ጋር ጠንካራ አጋርነት ይመሰርታል፤
- ልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ትግበራን ለማጠናከር ተጨማሪ ፈንድ ከለጋሾች ያፈላልጋል፤
- በተለያዩ ደረጃዎች ለሚገኙ አከናዋኞች/ፈፃሚዎች በልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምርት ዙሪያ የአጭር ጊዜ የአቅም ግንባታ ስልጠና በማዘጋጀት ይሰጣል፤
- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ዙሪያ ዓለም ዐቀፍና አገር አቀፍ የልምድ  ልወውጥ መድረኮችን ያደራጃል/ያዘጋጃል፤
- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን ትግበራ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤ ከሁኔታውም በመነሳት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
- የፖለቲካና የትምህርት አመራሩን፤የሃይማኖት መሪዎችን፤የአገር ሽማግሌዎችን እንዲሁም ማህበረሰቡን ባጠቃላይ በተለያዩ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳች ዙሪያ ቀጣይነት ባለው መልኩ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይረዳ ዘንድ የተሟላ የተግባቦት (communication guideline) መመሪያ ያዘጋጃል፡፡ ይህም መመሪያ በሁሉም ደረጃዎች መተግበሩን ያረጋግጣል፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀ ግብሮች ያዘጋጃል፤
- የአካቶ ትምህርትና ስልጠና ስርዓትን ሙሉ ትግበራ ለመጀመር የሚያመላክት/የሚያስችል ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤
- በትምህርት ስርዓቱ ሁሉም ደረጃዎች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን በተለይም የሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሻሻል የተለያዩ መንገዶችን/ዘዴዎችን ይቀይሳል፤ ለምሳሌ ተጨማሪ ትምህርት

ማስጠት (tutorial)፤ የኪስ ገንዘብ ማስጠት (pocket money)፤ የምክር አገልግሎት ማስጠት፤ ቁሳቁሶችን ማስጠት ( የሴቶች ንፅህና ማጠበቂያ፤ የፅህፈት መሳሪያዎች) ወዘተ፤

- በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የአካል ጉዳተኛ ሰልጣኞች የስልጠና ዕድል ለማስፋት ፤ ምቹ የስልጠና አካባቢን ለመፍጠርና የቅጥር ሁኔታቸውን ለማመቻቸት የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል፤
- የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተሳትፎ በማስናዶ ትምህርት ቤቶች፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፤ በመምህራንና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለማሳደግ አሁን እየተሰራበት ያለውን አዎንታዊ ድጋፍ (affirmative action) ያጠናክራል፤
- የአካቶ ትምህርት ብሄራዊ አሜ ኮሚቴ እንዲመሰረት ግንባር ቀደም ሚና መጫወት፤ ኮሚቴወም በአግባቡ ስራውን እንዲሰራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- በአገር አቀፍ ዓመታዊ የትምህርት ጉባኤ ላይ የልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ጉዳዮች በአግባቡ መቃኘታቸውን ያረጋግጣል፤

## 5.2. የክልልና የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ለመተግበር ማቀድ፤ በጀት መመደብና የስራ አሜራር ስርዓት ያደራጃል፤
- የአካቶ ትምህርት አቀራረብ በሁሉም የትምህርት ፕሮግራሞች ማለትም በቅድመ መደበኛ፤ በመጀመሪያ ደረጃ፤ በሁለተኛ ደረጃ፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፤ በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርትና በተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መካተቱትን ያረጋግጣል፤
- የልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ስትራረቴጂን በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ለመተግበር ከትምህርት ሚኒስቴርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤
- የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጡ መምህራንን በተዘዋዋሪ መምህርነት በጉድኝት ማዕከላትና ከተቻለም በየትምህርት ቤቱ እንዲሰሩ መመደባቸውን ያረጋግጣል፤
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያዎችን በክልል/በከተማ አስተዳደርና በዞን ክፍለ ከተማ ደረጃ ይመድባል፤
- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ሰልጥነው በክልሉና የከተማ አስተዳደሩ የሚገለግሉ መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን ለማፍራት የቅድመ ስራና የስራ ላይ ስልጠናን ያስተባብራል፤ ያደራጃል፤
- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ዙሪያ የአጭር ጊዜ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለዞንና ወረዳ አከናዋኞች ያዘጋጃል ይሰጣል፤

- ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበርን በየሩብ አመቱ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤ ከዚህም በተጨማሪ ከግምገማው ውጤት በመነሳት ድጋፍ ይሰጣል፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች መረጃ ጾታን መሰረት በማድረግ ለማሰባሰብ ስርዓት ማዘርጋትና ትምህርት ሚኒስቴር ለመረጃ ማሰባሰቢያ ካዘጋጃቸው መሳሪያዎች ጋር በማጣጣም መረጃውን ሰብስቦ ለትምህርት ሚኒስቴር ይልካል፤
- የአካቶ ትምህርት አቀራረብን በሁሉም የትምህርት አመራሮች የአቅም ግንባታና በመምህራን ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሀ ግብሮች ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጣል፤
- በልዩ ትምህርት ቤቶችና በልዩ ክፍሎች የሚሰሩ መምህራን በስራቸው ላይ እንዲተጉና እንዲቆዩ ከወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ጋር በመመካከር የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፤
- ከትምህርት ሚኒስቴርና ከሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር በክልሉ ለሚገኙ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የአካል ድጋፍ መሳሪያዎችና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አቅርቦት መኖሩን ያረጋግጣል፤
- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበር ላይ ድርሻ ካላቸው የተለያዩ አጋሮች ጠንካራ አጋርነት ይመሰርታል፤
- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበርን ለማጠናከር ተጨማሪ ፈንድ ከለጋሾች ያፈላልጋል፤
- የፖለቲካና የትምህርት አመራሩን፤ የሃይማኖት መሪዎችን፤ የአገር ሽማግሌዎችን እንዲሁም ማህበረሰቡን ባጠቃላይ በተለያዩ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮች ዙሪያ ቀጣይነት ባለው መልኩ በክልሉ ግንዛቤ ለማስጨበጥ በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የኮሙኒኬሽን መመሪያ በተግባር ላይ ያውላል፤
- የአካቶ ትምህርትና ስልጠና ስርዓትን ሙሉ ትግበራ ለመጀመር የሚያመላክት/የሚያስችል ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጉዳዮችን በተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ያካትታል፤
- በክልሉ በሚካሄዱ ሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ውስጥ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን በተለይም የሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሻሻል የተለያዩ መንገዶችን ይቀይሳል ለምሳሌ ተጨማሪ ትምህርት መስጠት (tutorial) የኪስ ገንዘብ መስጠት፤ ቁሳቁሶችን መስጠት (የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ፤ የፅህፈት መሳሪያዎች) ወዘተ፤

- የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተሳትፎ በማሳደግ ትምህርት ቤቶች፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናና በማሰልጠን ትምህርት ተቋማት ለማስፈፀም አሁን እየተሰራበት ያለውን አዎንታዊ ድጋፍ (affirmative action) ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በክልል ደረጃ የአካቶ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ እንዲቋቋም ማበረታታትና ስራውንም በአግባቡ እንዲሰራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- በክልሉ ዓመታዊ የትምህርት ጉባኤ ላይ የልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ጉዳዮች በአግባቡ መቃኘታቸውን ያረጋግጣል፤

## 5.3. የክልል/የከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ኤጀንሲ

- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ለመተግበር ማቀድ፣ በጀት መመደብና የስራ አመራር ስርአት ይዘረጋል፤
- በአካል ድጋፍ ማስጫ ጣቢያዎች፣ በትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችና አስፈላጊ በሆኑ ባለሙያዎች (የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያ/ተዘዋዋሪ መምህር፣ የስነ ልቦና ባለሙያና የምልክት ቋንቋ ተርጓሚ) የያዘ የድጋፍ ማስጫ ሜከላትን በክልሉ በሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ያደራጃል፤
- ከክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ዙሪያ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች የአጭር ጊዜ የአቅም ግንባታ ስልጠና በማዘጋጀት ይሰጣል፤
- በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ለአካል ጉዳተኛ ሰልጣኞች የስልጠና ዕድል ለማስፋትና ምቹ የስልጠና አካባቢን ለመፍጠር ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤
- ከአሰሪዎች/ቀጣሪዎች ጋር የምክክር መድረኮችን ከፍቶ በመወያየትነ በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ ግንዛቤያቸውን በማዳበር ለአካ ጉዳተኛ ምሩቃን የስራ ቅጥር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባር በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ወስጥ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህር ስትራቴጂ አተገባበርን በየሩብ ዓመቱ ክትትል ያደርጋል፣ ይገመግማል፤ ከግምገማው ወጤት በመነሳትም ድጋፍ ይሰጣል፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በፆታ በመለየት ለማሰብሰብ ስርዓት ማዘርጋትና ትምህርት ሚኒስቴር ለሚረጃ ማሰብሰቢያነት ባዘጋጃቸው መሳሪያዎች ወስጥ በማካተት ሚረጃውን ሰብስቦ ለትምህርት ሚኒስቴር ይልካል፤

- ከትምህርት ሚኒስቴር፤ ከክልል ትምህርት ቢሮዎችና ሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር በክልሉ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ወስጥ ልዩ ፍላጎት ላለላቸው ተሚዎች የትምህርት መረጃ ቁሳቁሶች አቅርቦት በበቂ ሁኔታ መኖሩን ያረጋግጣል፤
- በክልሉ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ወስጥ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን ለመተግበር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ አጋርነት ይመሰርታል፤
- በክልሉ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ወስጥ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበርን ለማጠናከር ተጨማሪ ፈንድ ከለጋሾች ያፈላልጋል፤
- የፖሊቲካና የትምህርት አመራሩን፤ የሃይማኖት መሪዎችን፤ የአገር ሽማግሌዎችን ቀጣሪዎችንና ማህበረሰቡን ባጠቃላይ በተለያዩ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮች ዙሪያ ቀጣይነት ባለው ሜኪኑ በክልሉ ግንዛቤ ለማስጨበጥ በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የኮሙኒኬሽን መመሪያ በተግባር ላይ ያውላል፤
- በክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ወስጥ የአካል ጉዳተኛ ሰልጣኞችን በተለይም የሴት አካል ጉዳተኛ ተሚዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ በጀት በመመደብ የተለያዩ መንገዶችን ይቀይሳል ለምሳሌ ተጨማሪ ትምህርት መስጠት (tutorial) የኪስ ገንዘብ መስጠት፤ ቁሳቁሶችን መስጠት (የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ፤ የፅህፈት መሳሪያዎች) ወዘተ፤እንዲሟሉ ያደርጋል፤
- በክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ወስጥ የአካል ጉዳተኛ ሰልጣኞችን የተሳትፎ ምጣኔ ለማሳደግ አዎንታዊ ድጋፍን (affirmative action) ተግባራዊ ያደርጋል፤

## 5.4. የዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ

- የልዩ ፍላጉት/አካቶ ትምህርትን ስትራቴጂ በዞኑ/ክፍለ ከተማው ለመተግበር ከክልሉ/ ከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤
- በስትራቴጂው አተገባበር ላይ ክትትል ያደርጋል፤ ከሁኔታዎችም በመነሳት ለወረዳዎች ድጋፍ ያደርጋል፤
- በዞኑ /ክፍለ ከተማው ወስጥ የሚገኙ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተሚዎች የአካል ድጋፍ መሳሪያዎችና እንዲሁም የትምህርት መረጃ ቁሳቁሶች ማግኘታቸውን ከክልሉ ትምህርት ቢሮ ጋር በቅርበት በመስራት ያረጋጋጣል፤

- ለስትራቴጂው ወጤታማ አተገባበር እንዲረዳ ለወረዳዎች ከክልሉ /የከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር የአጭር ጊዜ ስልጠና ይሰጣል፤
- በዞኑ/ክፍለ ከተማው የሚገኙ ልዩ ፍላት ያላቸው ተማሪዎች መረጃ እንዲሰበሰብ ያስተባብራል፤ የተሰበሰበውንም መረጃ ለክልሉ/የከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ በወቅቱ ይልካል፤

## 5.5. የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት

- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን በወረዳው ለመተግበር ያቅዳል፤ በጀት ይመድባል፤ የስራ አመራር ስርዓቱን ያደራጃል፤
- የአካቶ ትምህርት አቀራረብ በሁሉም የትምህርት ፕሮግራሞች ማለትም በቅድመ መደበኛ፤ በመጀመሪያ ደረጃ፤ በሁለተኛ ደረጃ፤ በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርትና በተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መካተቱትን ያረጋግጣል፤
- በወረዳው ወስጥ የልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን ከክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ከዞን/ ክፍለ ከተማ የትምህርት መምሪያና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤
- በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠነ ባለሙያ በጉድኝት ማዕከላትና በትምህርት ቤቶች ወስጥ በተዘዋዋሪ መምህርነት እንዲሰራ ይመድባል፤
- በድጋፍ መስጫ ማዕከላት ሊያገለግሉ የሚችሉ ብሬል የሚችሉና የሚያነቡ (ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህሀርት ቤቶች ብቻ) የምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎችን (ለመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) ከመምህራን ወስጥ በመመልመል የስራ ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
- በወረዳው የትምህርት ጽ/ቤት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያን ይመድባል፤
- በቅድሙ ስራ ላይ ስልጠና አማካይነት ሰልጥነው በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት በቅድሙመደበኛ ትምህርት በመጀመሪያ ደረጃና በድጋፍ መስጫ ማዕከላት የሚያገለግሉ ሰልጣኞችን ይመክማል፤
- በወረዳና በትምህርት ቤት ደረጃ ለሚገኙ ፈፃሚዎች በልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ዙሪያ የአጭር ጊዜ የአቅም ግንባታ ስልጠና አዘጋጅቶ ይሰጣል፤
- ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በወረዳው ወስጥ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት አተገባበርን በየሩብ ዓመቱ ክትትል ያደርጋል፤ ይገመግማል፤ከግምገማው ወጤት በመነሳትም ድጋፍ ይሰጣል፤
- በወረዳው ወስጥ የሚገኙ ልዩ ፍላጎት ያላቸዉን ተማሪዎች በቦታ በማየት መረጃ ለማሰብሰብ ስርዓት ማዘርጋትና ትምህርት ማኔስቴር ለመረጃ ማሰብሰቢያነት ባዘጋጃቸው መሳሪያዎች ወስጥ በማካተት መረጃዉን ሰብስቦ ለዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ ወይም ለክልሉ/የከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ይልካል፤

- የልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ጉዳይ በትምህርት ቤት ደረጃ በሚከሄደው ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሚሀ ግብር ወስጥ መግባቱን ይከታተላል፤
- በልዩ ትምህርት ቤቶችና በልዩ ክፍሎች ወሰጥ የሚሰሩ መምህራንን ለማትጋትና በስራቸው ላይ ለማቆየት በክልሉ ትምህርት ቢሮ የተዘረጋወን የማበረታቻ ስርዓት ይተገብራል፤
- የድጋፍ መስጫ ማዕከላትን በድጋፍ ሰጭ መሳሪያዎች (ተሽከርካሪ ወንበር፤ (wheel chair)፤ ነጭ በትር (cane)፤ የሚድመጫ መሳረያ (hearing aids) የአካል ድጋፍ መሳሪያ (cruthes)፤ የኮምፒዩተር ሶፍትዌር (JAWS) እንዲሁም ሌሎች ተገቢነታ ያላቸው የትምህርት ቁሳቁሶች ( ስሌት(slate)፤ ስታይለስ (styluses)፤ የብሬል ወረቀት፤ የምልከት ቋንቋ ማዝገበ-ቃላት) እንዲሁም በባለሙዎች (ተዘዋዋሪ መምህር፤ የስነልቦና ባለሙያ፤ የብሬል አሰልጣኝና የምልከት ቋንቋ ተርጓሚ ለማሟላት በጀት ይመድባል፤
- በወረዳው ወስጥ በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበር ላይ ድርሻ ካላቸው የተለያዩ አጋሮች ጋር ጠንካራ አጋርነትን ይመሰርታል፤
- በወረዳው ወስጥ የልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበርን ለማጠናከር ተጨማሪ ፈንድ ከለጋሾች ያፈላልጋል፤
- በወረዳው ወስጥ የማኅትን የፖለቲካና የትምህርት አመራሩን፤ የሃይማኖት መሪዎችን፤ የአገር ሽማግሌዎችንና ማህበረሰቡን በተለያዩ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮች ዙሪያ ቀጣይነት ባለው መልክ ግንዛቤ ለማስጨበጥ በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀወን የኮሚኒኬሽን መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በወረዳው ያለወን ክፍተት ለይቶ የእርምት እርምጃ በመወሰድና የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበርን ለማጠናከር የወቅታዊ ሁኔታ ትንተና (situation analysis) ያካሂዳል፤
- የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ (መጫወቻ ስፍራ፤ መንሸራተቻ (ramp) የወሃ ማጠጫ ቦታ፤ ሽንት ቤት፤ ቤተ መፃህፍት፤ አቅጣጫ አመላካች ወዘተ፤ ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽና ምቹ መሆኑን ያረጋግጣል፤
- በወረዳው ሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን በተለይም የሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሻሻል የተለያዩ መንገዶችን/ ዘዴዎችን/ ይቀይሳል፤ በትምህርት ቤት ደረጃ እንዲተገበሩም በጀት ይመድባል፤ ለምሳሌ ተጨማሪ ትምህርት መስጠት (tutorial)፤ የኪስ ገንዘብ (pocket money)፤ የማማከር አገልግሎት፤ የጽ/መሳሪያዎች፤ የንፅህና ማጠበቂያ (modes) ወዘተ፤
- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮች በቅድመ-መደበኛና በስራ ላይ ስልጠና አማካይነት በጎልማሶች ትምህርት አመቻቾች ስልጠና ፕሮግራም መካተቱን ያረጋግጣል፤

- የድጋፍ መስጫ ማእከላት በአጎራባች ለሚገኙ የጎልማሶች ትምህርት ጣቢያዎች ድጋፍ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮች በወረዳው ዓመታዊ ጉባዔ ላይ በአግባቡ መቃኘታቸውን ያረጋግጣል፤

## 5.6. የወረዳ/ቀበሌ የትምህርትና ስልጠና ቦርድ

- የአካባቢ ሀብትን በማሰባሰብ ለልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ትግበራ እንዲውል ያደርጋል፤
- ከወረዳ ት/ጽ/ ቤት ጋር በመተባበር የፖለቲካ፤ የሃይማኖትና የማህበረሰብ መሪዎች እንዲሁም ማህበረሰቡን በአካ ጉዳተኝነት ጉዳዮችና በአቶ ትምህርት ዙሪያ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ያከናውናል፤
- በአጥቢያ የሚገኙ አካል ጉዳተኛ ህፃናትን ቆጠራ (sensus) ስራ ያተባብራል፤ የአካል ጉዳተኛ ህፃናት ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ የቅስቀሳና የማነሣሣ ስራ ያከናውናል፤

## 5.7.ትምህርት ቤት

### 5.7.1. የትምህርት ቤት አመራር

- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን በትምህርት ቤት ደረጃ ወጠቃማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የሚያስችል ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ለዕቅዱ ማስፈፀሚ በጀት ይመድባል፤
- የትምህርት ቤት አካባቢ (physical environment) የመጫወቻ ሜዳ፤ መንሸራተቻ (ramp) ፤የሚጠጥ ወሀ አቅርቦት፤ መጸዳጃ ቤት፤ ቤተ መጸሀፍት፤ አቅጣጫ አመላካች (signage)፤ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ምቹና ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ በተለይም አካል ጉዳተኛ ሴት ተማሪዎች ተስማሚ የመፀዳጃ ቤት አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤
- መደበኛ የክፍል መምህራን ከተዘዋዋሪ መምህራን ሙያዊ ድጋፍ እያገኙ በተለያዩ ደረጃዎችና ሁኔታዎች የሚገኙ ተማሪዎችን በማየትና በመመዘን የመማር ፍላጎታቸውን ማሟላት የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በተለይ አካል ጉዳተኛ ሴት ተማሪዎች እንዳስፈላጊነቱ የቲቶሪያል፤ የኢኮኖሚ (የኪስ ገንዘብ)፤ የቁሳቁስ (የጽ/መሳሪያ፤ሞዴስ) የጋይዳንስና ካውንስሊንግ ወዘተ ድጋፎችን የሚያገኙበትን ብሎም የትምህርት ተሳትፏቸውንና ወጠቃማነታቸውን የሚጎለብቱበትን ስልት ይነድፋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤

- እንዳስፈላጊነቱ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የነፍስ-ወከፍ ትምህርት መርሀግብር እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ያስተባብራል፤
- እንደ ብሬል ወረቀት፣ ስሌት (slate) ስታይለስ (styluses) ነጭ በትር (cane) የምልክት ቋንቋ መዝገበ ቃላት (sign language dictionary) ላሉ የትምህርት ቁሳቁሶች መግዣ በጀት ይመድባል፤ ግዥውን ይፈፅማል፤ ቁሳቁሶችን ጥቅም ላይ ያውላል፤
- የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት የፖሊቲካ፣ የማህበረሰብ እና የሃይማኖት መሪዎች፣ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ፣ የወላጅ-መምህር -ተማሪ ህብረት አባላትና ወላጆች

  በተለያዩ የልዩ ፍላት ትምህርት ጉዳዮች (አካል ጉዳተኛ ህፃናት ስላሏቸው ዕምቅ ችሎታዎች፣ እነዚህን ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት የመላክና በትምህርታቸው እንዲዘልቁ የማድረግ አስፈላጊነት፣ ወዘተ) ላይ ግንዛቤ እንዲጨበጡ ያደርጋል፤የትምህርት ቤት ሚ ሚዲያ፤ ትምህርት ቤቱ ከወላጆችና ከማህበረሰቡ ጋር የሚደርጋቸው ልዩ ልዩ ስብሰባዎች፣ በትምህርት ቤት ደረጃ የሚዘጋጁ የትያትርና የድራማ ፕሮግራሞች፣ ወዘተ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ፤
- የተሻለ የትምህርት ውጤት የሚያስመዘግቡ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚሸለሙበት ስርዓት በማዘርጋት ለበለጠ ውጤት እንዲተጉና ለሌሎች አቻዎቻቸው ተምሳሌት እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- ከቀበሌ አስተዳደርና የትምህርትና ስልጠና ቦርድ ጋር በመሆን በአካባቢ ማህበረሰቦች የሚገኙ አካል ጉዳተኛ ህፃናትን ቆጠራ ስራ ያደራጃል፤ ያስተባብራል፤ ህፃናቱ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡም ወላጆቻቸውን የመቀስቀስና የማሳመን ስራ ያከናውናል፤
- በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያለቸውን ተማሪዎች ስታቲስቲካዊ መረጃ በመደበኛነት በሚሰባሰብባቸው መጠይቆች ወስጥ ያካትተታል፤ መረጃውን ለወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ይልካል፤
- ተገቢነት ያላቸው ድጋፎች በመስጠትና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመስራት ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የትምህርት ማቋረጥና ክፍል የመድገም ማጠን እንዲቀንስ በሂደትም እንዲወገድ ጥረት ያደርጋል፤
- የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን በትምህርት ቤት ደረጃ በመፍጠርና ተጨማሪ ሀብት ከለጋሾች የሚገኝበትን ስልት ነድፎ በማንቀሳቀስ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን ትግበራ ያጠናክራል፤
- የትምህርት ቤቱ አመራር መምህራንና ወላጆች ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ወስጥ በሚያጋጥሟቸው ችግሮች ላይ የሚወያዩበትና የጋራ መፍትሄዎች የሚፈልጉበትን መደበኛ የምክክር ስብሰባ ጊዜ እንዲኖር ያቅዳል፤
- መምህራን የተማሪዎቻቸውን የትምህርት ቅስሞሽ ችግሮች በመለየትና የመፍትሄ ሃሳቦችን በማመንጨት ላይ የሚያተኩሩ ተግባራዊ የጥናትና ምርምር ስራዎችን እንዲያካሂዱ ያበረታታል፤

- በትምህርት ቤት ደረጃ በሚከሄደው ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም ወስጥ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮች መካተታቸወን ያረጋግጣል፤
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ባላቸው ተማሪዎች ወላጆችና በትምህርት ቤት መካል ጠንካራ ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋል፤ ወላጆች ለልጆቻቸው ትምህርት አስፈላጊወን ድጋፍ የሚድረግ ሃላፊነታቸወን እንዲቀበሉና በተግባር እንዲወጡ ያበረታታል፤
- መደበኛና ተዘዋዋሪ መምህራን የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን ከመተግበርና የሁሉንም ህፃናት የትምህርት ፍላጎቶች ከማሟላት አኳያ የተሰጧቸው ሃላፊነቶችና ግዴታዎች ባግባቡ መወጣታቸወን ያረጋግጣል፤
- የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ፤ ወላጆችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በየመንፈቅ ዓመቱ እየተሰባሰቡ ትምህር ቤቱ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን በመተግበር ረገድ ያከናወናቸወን ስራዎች በጋራ የሚገመግሙበት መድረክ ያዘጋጃል፤
- የትምህርት ቅስሞሽ ችግሮችን ለመለየትና አስፈላጊወን ድጋፍ ለተማሪዎች መስጠት ይቻል ዘንድ በአገር ዐቀፍ ደረጃ የተዘጋጁ የመለያና የምዘና መሳሪያዎች ስራ ላይ መዋላቸወን ያረጋግጣል፤ ከዚህ አኳያ የተጠናቀሩ የተማሪዎች ነፍስ-ወከፍ መረጃዎችም በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፤
- በትምህርት ቤቱ የሚገኙ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቁሳቁሶች ዓይነትና ብዛት መዝግቦ ይይዛል፤ እነዚህ ቁሳቁሶች ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሰጧቸወን ግልጋሎቶችና በተማሪዎቹ የትምህርት ቅስሞሽ ላይ ያስገኟቸወን ወጤቶች የሚየመለከት ሪፖርት በማዘጋጀት ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና ለወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ያቀርባል፤
- የሁሉንም ተማሪዎች የትምህርት ፍላጎት ማሟላት ይቻል ዘንድ በአገር ዐቀፍ ደረጃ የተዘጋጀው የስርዓተ ትምህርት ማስማሚያ አተገባበር መመሪያ ስራ ላይ ያወላል፤
- በአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችና በጉዳት አልባ አቻዎቻቸው መካከል ጠንካራ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ትስስር ለመፍጠር ይቻል ዘንድ የአካል ጉዳት ክበብ በትምህርት ቤቱ እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ ለክለቡ የስራ እንቅስቃሴ የሚየስፈልገወንም የቁሳቁስና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፤
- ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ወደሚቀጥለው ክፍል የሚያደርጉት የተፋጠነ ዝወወር (accelerated promotion) ትምህርት ሚኒስቴር ባዘጋጀው የስርዓተ ትምህርት ማስማሚያ አተገባበር መመሪያ መሰረት ሚፀማ ያረጋግጣል፤
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የትምህርት ቅስሞሽ ምዘና ከአካል ጉዳታቸው ዓይነት ጋር በተገናዘበ ሜሎኩ ሚፀማ ያረጋግጣል፤ (ለምሳሌ አንድ ዓይነ- ስወር ተማሪ በቃል ፈተና ወይም በቴፕ ሪከርደር በተቀረፀ ፈተና አማካኝነት ሊማዘን ይችላል፡፡ መስማት የተሳነው ተማሪ ደግሞ በምልክት ቋንቋ እየተደገፈ ሊማዘን ይችላል፡፡ የመሚር ችግር ያለበት ተማሪም ከመደበኛው የበለጠ ተጨማሪ የፈተና ጊዜ ሊያስፈልገው ይችላል፤ አሊያም በአንድ ቀን ወስጥ አንድ ፈተና

ብቻ እንዲወስድ ሊደረግ ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨሜሪ፤ እንደ ፖርትፎሊዮ የፕሮጀክት ስራ፤ ግለ-ምዝና፤ ምልከታ ያሉ የተከታታይ ምዝና ዘዴዎች በተጨማሪነት ወይም በአማራጭነት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

## 5.7.2. የመደበኛ ክፍል ማማህር

- በማማህራን ትምህርት ተቋማት ቆይታወና በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ መርሀ ግብር አማካኝነት በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ላይ የተሰጠትን ስልጠናዎች መሰረት በማድረግ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ድጋፍ ይሰጣል፤
- ከአቅሙ በላይ የሆኑ ችግሮች ሲያጋጥሙት የተዘዋዋሪ ማማህሩን በማማከር እንዲቃለሉ ያደርጋል፤
- ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸወን ተማሪዎች የትምህርት ቅስሞሽ ለማስለጥ ከወላጆች ጋር በቅርብ በመመካከር ይሰራል፤
- በመማር-ማስተማሩ ሂደት የሚያጋጥሙ የትምህርት ቅስሞሽ ችግሮችን ለመቅረፍ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤
- የተማሪዎች የነፍስ-ወከፍ ችሎታ እንዲሁም የትምህርት ቅስሞሽና አካባቢያዊ ችግሮችን በማየትና በመመዘን ችገሮቹ የሚቃለሉበትን መንገድ ያቅዳል፤ አስፈላጊወን ድጋፍም ይሰጣል፤
- በክፍል ወስጥ የሚገኙትን የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎቶች ለማርካት ፈጠራ በማከል የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይጠቀማል፤ ለምሳሌ፤ በትብብር መማማር፤ የአቻ መማማር፤ ወዘተ ቡድን ምስረታ ( በችሎታ ላይ በመመስረት፤ በመቀላቀል፤ በፍላጎት ላይ በመመስረት) ናቸው፡፡

## 5.7.3. የድጋፍ መስጫ ማዕከል

በአጠቃላይ ሲታይ ድጋፍ መስጫ ማዕከላት ለማማህራን፤ ለት/ቤት አስተዳደር፤ ለወላጆችና ለነፍስ-ወከፍ ተማሪዎች ሙያዊ ድጋፍ ከመስጠታቸው ባሻገር ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ምቹ የድጋፍ መሳሪያዎችን፤ የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን፤ የማድመጫ መሳሪያዎችን ወዘተ ያቀርባሉ፤ በዚህ በድጋፍ መስጫ ማዕከል ወስጥ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ድጋፍ የሚያደርጉ የተለያዩ ባለሙያዎች ማለትም ተዘዋዋሪ ማማህራን የስነ-ልቦና ባለሙያዎች፤ የብሬል አሰልጣኞች፤ የምልክት ቋንቋ አሰልጣኞችና ተርጓሚዎች ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ ባለሙያዎች ሃላፊነትና የስራ ድርሻ ከዚህ በተቻ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 5.7.3.1. ተዘዋዋሪ ማማህር

- በትምህርት ቤት ደረጃ ልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን ለመተግበር የትምህርት ቤቱ አመራር ዕቅድ ሲያወጣ በጀት ሲመድብ ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
- በአጎራባች የጎልማሶች የትምህርት ጣቢያዎች ለሚገኙ አካል ጉዳተኛ ጎልማሶችና አመቻቾች ቴክኒካዊና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
- የመደበኛው ክፍል መምህራን በክፍላቸው ወስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎቶች ለሟካት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘደዎችን (ለምሳሌ በትብብር መማር፤ የአቻ መማማር፤ ወዘተ በቡድን ምስረታ (በችሎታ ላይ፤ በመቀላቀል፤ በፍላጎት ወዘተ) እንዲጠቀሙ ስልጠናና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
- መምህራን የተማሪዎችን የነፍስ ወከፍ የትምህርት ቅስሞሽ ችሎታ እንዲመዝኑና አካባቢያዊ እንቅፋቶችን እንዲለዩ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ተማሪዎቻቸውን ለመርዳት የታዩትን እንቅፋቶች ለማስወገድ እንዲያቅዱ ይረዳቸዋል፤
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ክፍል ወስጥ በመግባት የክፍል መምህሩን ይረዳሉ፤ ከዚህም በተጨሪ፤ ከፍተኛ የመማር ችግር ያጋጠማቸውን ተማሪ ወይም ተማሪዎች ወደ ድጋፍ መስጫ ማዕከል በመውሰድ ተጨሪ ድጋፍ ይሰጣል፤
- የነፍስ-ወከፍ የትምህርት መርሀ ግብር ከሚያወጣው ቡድን ጋር በቅርበትና በትብብር ይሰራል፤
- በድጋፍ መስጫ ማዕከሉ አቅራቢያ ከሚገኙ የማስረተ-ማህበረሰብ ተሃድሶ (CBR) አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በትብብር ይሰራል፤

### 5.7.3.2. የስነ ልቦና ባለሙያ (ለ2ኛ ደረጃ)

- በትምህርት ቤቱ ለሚገኙ ሁሉም ተማሪዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ጨምሮ የጋይዳንስና ካወንስሊንግ አገልግሎት ይሰጣል፤
- መምህራን የተማሪዎችን የነፍስ-ወከፍ የትምህርት ቅስሞሽ ችሎታ እንዲመዝኑና አካባቢያዊ እንቅፋቶችን እንዲለዩ ድጋፍ ያደርጋል፤ መምህራንም ከዚህ በመነሳት ተማሪዎቻቸውን ለመርዳት የታዩትን እንቅፋቶች ለማስወገድ እንዲያቅዱ ይረዳቸዋል፤
- ለሁሉም ወላጆች ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ወላጆች ጨምሮ አስፈላጊውን የጋይዳንስና የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፤

### 5.7.3.3. የብሬል አሰልጣኝ (ለመጀመሪያ ደረጃ)

- በሳተላይትና ጉድኝት ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ዓይነ-ስወራን ተማሪዎች በብሬል ማፃፍና ማንበብ እንዲችሉ ስልጠና ይሰጣል፤

- በሳተላይትና ጉድኝት ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ መምህራን በብሬል ማፃፍና ማንበብ እንዲችሉ ስልጠና ይሰጣል፤
- በሳተላይትና በጉድኝት ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ዓይነ-ስውራን ተማሪዎች የእንቅስቃሴ ትውውቅ (orientation and mobility) ስልጠና ይሰጣል፤
- ተመጣጣኝ ክፍለ ጊዜ ተሰጥቶት እንደ መደበኛ መምህር ያስተምራል፤

### 5.7.3.4. የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ

- በሳተላይትና በጉድኝት ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ማስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የምልክት ቋንቋ ስልጠና ይሰጣል፤
- በሳተላይትና ጉድኝት ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ መምህራን የምልክት ቋንቋ ስልጠና ይሰጣል፤
- በሳተላይትና ጉድኝት ትምህርት ቤቶች ማስማት የተሳናቸው ልጆቻቸውን ለሚያስተምሩ ወላጆች የምልክት ቋንቋ ስልጠና ይሰጣል፤
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለወላጆች፣ ለትምህርት ቤት አመራርና ለመምህራን የምልክት ቋንቋ ትርጉም አገልግሎት ይሰጣል፤
- ተመጣጣኝ ክፍለ ጊዜ ተሰጥቶት እንደ መደበኛ መምህር ያስተምራል፤

### 5.7.3.5. የልዩ ትምህርት ቤት/ክፍል መምህር

- የተጠናከረ ድጋፍ የሚፈልጋቸውን ከፍተኛ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች በትናንሽ ቡድኖች እየከፋፈለ ያስተምራል፤
- የልጆቹን የትምህርት ቅስማሽ (ባህርይ፣ ማህበራዊ፣ ቋንቋ፣ ስሜት፣ የግል ንፅህና አጠባበቅ፣ ማገናዘብ ክሂሎት) ለማዳበር ስርዓተ ትምህርቱን ያስማማል፣ የትምህርት አቀራረቡን ያሻሽላል፤
- አስረጂ (resource person) በመሆን ለሌሎች መምህራንና ትምህርት ቤቶች ያገለግላል፤ ይህም በልዩ ፍላጎት ትምህርት ያለውን ዕውቀትና ክህሎት ለሌሎች በማካፈል አካቶ ትምህርትን ለማጠናከር ይረዳል፤
- ከሌሎች ባለሙያዎች (የነፍስ-ወከፍ የትምህርት ሚርሀግብር ቡድን፣ የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኛ (community worker)፣ ወጌሻ) ጋር በመተባበር ይሰራል፤

### 5.7.3.6. ወላጆች

- ከትምህርተ ቤቱና ከመምህራን ጋር በቅርበት በመስራት ስለልጃቸው ባህርይ፣ ጥንካሬና ችሎት መረጃ ይሰጣሉ፤

- ለልጃቸው በቤት ውስጥ ማህበራዊ፣ አካላዊ፣ ስነልቦናዊና በትምህርቱ ዙሪያ እና ወደ ትምህርት ቤት ሲጓዝ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ፤
- ለሚኖሩበት ማህበረሰብ የልጃቸውን ጠንካራ ጎኖችና የተለያዩ ችሎታዎች (talents) ይገልፃሉ (ያስተዋውቃሉ)፤ ለምሳሌ የልጁን የፈጠራ ችሎታ፤ በአርት ፤በስፖርት ወዘተ ያለውን ችሎታ፤
- በነፍስ-ወከፍ የትምህርት ሚሀ ግብር ቡድን ወስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፤

## 5.8. የጎልማሶች ትምህርት ጣቢያ

- አስፈላጊውን የትምህርት ቁሳቁሶችና የጽህፈት መሳሪያዎች (ስሌት፤ ስታይለስ፤ የብሬል ወረቀት፤ የምልከት ቋንቋ ማዝገበ ቃላት፤ ወዘተ) ለጎልማሳ አካል ጉዳተኞች ያቀርባል፤
- አካል ጉዳተኛ ጎልማሶችን በትምህርታቸው ለሚደገፍ በአቅራቢያ ከሚገኙ የድጋፍ መስጫ ሜከላት ቴክኒካዊና የሙያ ድጋፍ ይጠይቃል፡፡

## 5.9. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ

- አካል ጉዳተኛ ሰልጣኞችንና አሰልጣኝ ማምህራንን ሊያግዝ የሚችል የድጋፍ መስጫ ሜከል ያደራጃል፤
- የጉድኝት ሜከላቱን በተፈላጊው የትምህርት መሳሪያዎችና ሚጃ መሳሪያዎች እንዲሁም በሰው ሃይል የማሟላት ተግባር ያከናወናል፤
- በኮሌጁ ለስልጠና የሚገቡ ሰልጣኝ አካል ጉዳተኞችን የስልጠና ተግዳሮቶች ሊፈታ የሚችል የጥናትና ምርምር ስራ ያከናወናል፤
- የኮሌጁ መማሪያ አካባቢ (መጫወቻ ስፍራዎች፤ መወጣጫ የወሀ አቅርቦት፤ መፀዳጃ ስፍራዎች፤ ቤተ ማህፍት) ወዘተ አካ ጉዳተኛ ሰልጣኞችንና በተለይም ሴት አካል ጉዳተኞች ሰልጣኞችን ሊያገለግሉ በሚችል ሜኩ መደራጀቱን ያረጋግጣል፤
- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ዙሪያ ለኮሌጁ ማህበረሰብ የግንዛቤ ማስፋፊያ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ይሰጣል፤
- በኮሌጁ የተመደቡ ማምህራን በወሰዱት ስልጠና ላይ በመንተራስ አካል ጉዳተኞች ሰልጣኞችን ሚደገፋቸውን ይከታተላል፤
- የአካል ጉዳተኛ ሰልጣኞችን በተለይም ደግሞ ሴት ሰልጣኝ አካል ጉዳተኞችን በትምህርት ለማገዝ (tutorial)፤ የኪስ ገንዘብ (pocket money)፤ የማማከር አገልግሎት፤ የጽ/መሳሪያዎች፤ የንፅህና ማጠበቂያ (modes) ወዘተ የሚሟሉበት መንገድ ያፈላልጋል፤

## 5.10. ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ

- በተቋሙ ወስጥ በሚሰጠው የትምህርት ፕሮግራምና ስርዓተ ትምህርት የአካቶ ትምህርት ፅንሰ–ሃሳብን ያካተተ የትምህርት አቀራረብና ዘዴን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፤
- የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት በሚያሟላ መንገድ ማስተማር ይችሉ ዘንድ ለመላው የተቋሙ መምህራን የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በአካቶ ትምህርት አቀራረብና አሰጣጥ ዘዴ ዙሪያ ያደራጃል፤
- የክልሉንም ሆነ የአገሪቱን ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ስልጠና ማካሄድ የሚችሉ ዲፓርትመንቶች በሙሉ አቅም መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤
- ተቋማቱ የሚያስመርቋቸው ሰልጣኞቹ ተግባራዊ ክህሎትን አዳብረው ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች በክፍል ወስጥ ተገቢውን እገዛ ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፤
- ተመራቂዎች በዲፕሎማም ሆነ በዲግሪ ደረጃ ከተቋማቱ ተመርቀው በሚወጡበት ወቀት የተጠናከረ የንደፈ–ሃሳብና የተግባር ክህሎት ታጥቀው በጉድኝት ማዕከላትና በትምህርት ቤቶች ወስጥ ለአካቶ ትምህርት ትግበራ ዕወን ማሆን የሚያስችል ደረጃ ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ተገቢውን ስልጠና የሚሰጡ አግባብነት ያላቸው ባለሙያዎች ይበልጥ ለማጠረታታት ደረጃቸውን የሚያሳድጉበት መንገድ ያመቻቻል፤
- ለተቋሙ ህብረተሰብ በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ያደራጃል፤
- ለተቋሙ አሰልጣኞችና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ድጋፍ መስጫ የሚያገለግሉ የጉድኝት ማዕከላት መቋቋማቸውን ያረጋግጣል፤
- ተቋሙ በአስፈላገው የትምህርት መሳሪያዎችና ድጋፍ መስጫዎች እንዲሁም ባለሙያዎች (ተዘዋዋሪ መምህራን፤ የስነ ልቦና ባለሙያዎች፤ የብሬል አሰልጣኞችና የምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎች) መሟላታቸውን ይከታተላል፤
- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ዙሪያ ፖሊሲ ለመቅረፅና በአዳዲስ ግኝቶች ዙሪያ የተጠናከረ ስራ መስራት የሚያስችል የምርምር ስራዎች የሚካሄዱበትን መንገድ ያመቻቻል፤
- የምርምር ወጤቶችንና ግኝቶችን በአገር አቀፍና ዓለም ዐቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅ የሚያስችል የህትመትና ስርጭት ስራ ያከናወናል፤
- በተቋሙ መማሪያ አካባቢዎች (መጨወቻ ስፍራዎች፤ መወጣጫ የወሀ አቅርቦት፤ መፀዳጃ ስፍራዎች፤ ቤተ መፃህፍት) ወዘተ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችንና በተለይም ሴት አካል ጉዳተኞች ተማሪዎችን ሊያገለግሉ በሚችል መልኩ መደራጀቱን ያረጋግጣል፤

- የአካል ጉዳተኛ ተሜዎችን በተለይም ደግሞ ሴት አካል ጉዳተኞችን በትምህርት ለማገዝ (tutorial)፤ የኪስ ገንዘብ (pocket money)፤ የማማከር አገልግሎት፤ የጽ/መሳሪያዎች፤ የንፅህና ማጠበቂያ (modes) ወዘተ የሚቻሉበት መንገድ ያፈላልጋል፤

# 6. የሌሎች ባለድርሻ አካላት ሚና

## 6.1. የአካቶ ትምህርት ብሄራዊ አማካሪ ኮሚቴ

- ብሄራዊ አማካሪ ኮሚቴው አባላት የሚከተሉት ናቸው፤

የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሄራዊ ማህበራት ፌዴሬሽን፤ የኢትዮጵያ ዓይነ-ስውራን ብሄራዊ ማህበር፤ የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሄራዊ ማህበር፤ የኢትዮጵያ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ብሄራዊ ማህበር፤ የኢትዮጵያ ጉዳተኛ ሴቶች ብሄራዊ ማህበር፤ የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ብሄራዊ ማህበር፤ የኢትዮጵያ መስማት -ማየት የተሳናቸው ብሄራዊ ማህበር፤ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፤ ትምህርት ሚኒስቴር፤ የማሰረተ ማህበረሰብ ተሃድሶ ሚብ በኢትዮጵያ፤ ክሮስቶፎር ብላይንደን ሚሽን፤ አዲስ ደቨሎፕመንት ቪዥን፤ ኮተቤ ማማህራን ትም/ ኮሌጅ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ዩኒሴፍ፤ ዩኔስኮና የፊንላንድ ህፃናት አድን ድርጅት ናቸው፡፡

- ኮሚቴው የሚከተሉት ሚናዎች ይኖሩታል፤
  - በአገር ዐቀፍ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂና የስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ላይ አስተያየት ይሰጣል፤
  - በክትትልና ግምገማ ተግባራት ዙሪያ ይሳተፋል፤
  - የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው እንዲሻሻል የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፤ በተጨማሪም ለስትራቴጂው አተገባበር የወሳኔ ሰጪዎች ድርሻቸውን እንዲወጡ ያሳስባል፤
  - በአካቶ ትምህርት ትግበራ ላይ አስተያየቱን ይሰጣል፤ እንዲሁም በአገር ዐቀፍ ዓመታዊ የትምህርት ጉባኤ ላይ ይሳተፋል፤

## 6.2. የሚኒስቴር መ/ቤቶች

የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበር ላይ ከዚህ ቀጥሎ የተገለፁት የሚኒስቴር መ/ቤቶች ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የድርሻቸውን እንደሚወጡ ይጠበቃል፡፡

- ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ኮንቬንሽንን (2006 እ.ኤ.አ) ይተገብራል፤

- ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር- ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከጤና ጋር በተያያዘ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
- የሴቶች፤ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር- ከአካል ጉዳተኛ ሴት ተማሪዎች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮችን ለመቃለል ይሰራል፤
- የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር- የህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2009 በተግባር ላይ መዋሉንና የት/ቤት ህንፃዎች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

## 6.3. የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች፤ ለጋሾችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

- በአጭርና በረዥም ጊዜ ስትራቴጂያዊ ዕቅዶችና በአካቶ ትምህርት ትግበራ ይሳተፋሉ፤
- በተለያዩ ደረጃዎች ለሚገኙ የአካቶ ትምህርት ፈፃሚዎች ምክርና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣሉ፤
- በሚያካሂዷቸው የትምህርት ሙከራ ግብሮች ወስጥ የአካቶ ትምህርት የተግባር ልምዶችን ያካትታሉ፤
- በአካቶ ትምህርት ትግበራ በምሳሌነት ከሚጠቀሱ አገሮች የልምድ ልውውጥ ጉብኝት እንዲደረግ በፋይናንስ ይረዳሉ፤
- በተለያዩ ደረጃዎች በልዩ ፍላጎት ትምህርት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጥ ተግባራት እንዲከናወኑ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣሉ፤
- የድጋፍ መስጫ ማእከላትን ለማደራጀት የድጋፍ ሰጪ መሳሪያዎችንና የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን ያሟላሉ፤

## 6.4. የአካል ጉዳተኞች ፌደሬሽንና ብሄራዊ ማህበራት

- የአካቶ ትምህርት ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ሲዘጋጅና እንዲሁም በትግበራው ወቅት በክትትልና ግምገማ ይሳተፋል፤
- የአካቶ ትምህርት አተገባበርን ለማሻሻል የሚረዳ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን በተለይም የአካል ጉዳተኞችን ትምህርት አስመልክቶ ለወሳኔ ሰጪ አካላት ግንዛቤ ለማስጨበጥ ጥረት ያደርጋል፤

- በተለያዩ ደረጃዎች ከሚገኙ የትምህርት አመራር አካላት ጋር በመተባበር ማህበረሰቡን በተለያዩ የአካል ጉዳተኝነት ጉዳዮችና በአካቶ ትምህርት የተግባር ልምድ ዙሪያ ግንዛቤ በማስጨበጥ አካል ጉዳተኛ ልጆች ያላቸው ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ለማነሳሳት ጥረት ያደርጋል፤
- በሚዲያ አሰባሰብ፤ በኢንፎርሜሽን ልውውጥና ስርጭት ወስጥ ይሳተፋል፡፡